# ኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ምንድነው?

ኮሮናቫይረስ (በሌላ አጠራር ኮቪድ-19 ወይም COVID-19 የሚባለው) ከዛሬ ዓመት ጀምሮ እስከአሁኑ ሰዓት እየተዛመተ የሚገኝ አዲስ ህመም ነው። በዓለም ዙሪያ አበይት የሆኑ ችግሮችን ፈጥሯል።



በርካታ ሰዎች ቤታቸው ሆነው እረፍት በማድረግ ከኮሮናቫይረስ ይድናሉ፤

ዳሩ ግን አንዳንድ ሰዎች ላይ ስለሚበረታባቸው ህመሙ ሊከብድ ወይም እስከሞት ሊያደርሳቸው ይችላል።







**አንዳንድ የኮሮናቫይረስ ምልክቶች፡**



እንደአዲስ የሚያጋጥም ሳል እና የሳል ሁኔታው ሳይቋረጥ ሲቀጥል




ከፍተኛ የሰውነት ሙቀት




የማሽተት ወይም የመቅመስ ስሜትዎ ሲጠፋ ወይም ሲቀየር

ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች ካሉብዎት፥ ባሉበት ቦታ ሆነው ይቆዩ፣ ወደውጬ አይውጡ። የምርመራ ቀጠሮ ለመያዝ በስልክ ቁጥር 119 ይደውሉ ወይም www.gov.uk/get-coronavirus-test የሚለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ።






እኛ ሁላችንም በምንንቀሳቀስበት ጊዜ ፊታችንን በመሸፈን፣ ከሌሎች ጋር ያለንን አካላዊ ቅርርብ በማራራቅ፣ እና እጃችንን በመደበኛነት በመታጠብ የኮሮናቫይረስን ስርጭት ማስቆም አለብን።



**እርስዎን ኮሮናቫይረስ የሚጠብቅዎት ክትባት የተገኘ መሆኑ አንድ የምስራች ነው።**

ክትባቱን ለመከተብ ወይም አለመከተብ የራስዎ ምርጫ ቢሆነም፥ ቢከተቡ እጅግ ይመከራል። ስለክትባቱ ተጨማሪ መረጃዎችን በዚህ ገጽ ሌላኛው ጎን ላይ ያገኛሉ።

Nottingham City Council

# ስለኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) ክትባት

የኮሮናቫይረስ ክትባት በመርፌ የሚሰጥ ነው፤




ክትባቱን በ2 ዙር መርፌ በመወጋት የሚወሰዱ ሲሆን፣ ይህም በ3 እስከ 12 ሣምንታት ልዩነት ይደረጋል።




ክትባቱ የማያሰጋ መሆኑን ለማረጋገጥ ፍተሻ ተደርጎበታል።



የኮሮናቫይረስ ክትባት **ምንም የእንስሳት ተዋፅዖ የለበትም።**



**ክትባቱን እርስዎ በመውሰድዎ፥ ራስዎን ከኮሮና ቫይረስ ይከላከላሉ።**

ከክትባቱ ኮሮናቫይስ አይያዙም።



ክትባቱን ማግኘትዎ በኮሮናቫይረስ የከፋ ህመም የማጋጠሙን ዕድል ይቀንስልዎታል።



ቫይረሱ እንዳይይዝዎት ሊያደርግ ወይም ለሌላ ሰው እንዳያስተላልፉ ስለማድረግ አቅሙ እስካሁን ለማወቅ አልቻልንም።



ከክትባቱ ኮሮናቫይረስ አይይዝዎትም፥ ዳሬ ግን ክንድዎ ላይ የመዛል ስሜት ሊኖርዎ ይችላል። መርፌውን ከተወጉ በኋላ ከ1-2 ቀናት ያህል ጉንፋን እንዳመመዎት ዓይነት የህመም ስሜት ቢኖርብዎት ችግር የለውም። ይህ ማለት የእርስዎ አካላት ኮሮናቫይረስን ስለሚያጠቁበት ሁኔታ ከክትባቱ እየተማሩ ነው ማለት ነው።

ክትባቱ ወዲያውኑ መከላከል እንዲችሉ አቅም አይሰጥዎትም። ሥራውን ለመጀመር በርካታ ሣምንታት ይፈልጋል። የተሻለ የመከላከል አቅም እንዲኖርዎት ሁለቱንም ዙር ክትባት ማግኘት አለብዎት።

**ዳሩ ግን፥ በዚያውም ጊዜ ቢሆን ደህንነትዎን ለመጠበቅ፥ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላም እነዚህን በማድረግ ይቀጥሉ፡**



ከሌሎች ሰዎች ራቅ ይበሉ (ማህበራዊ ርቀትን መጠበቅ)



የፊት ጭምብል ማድረግ



በተደጋጋሚ እጅን መታጠብ